UNOFFICIAL TRANSLATION

# የስቶክሆልም መግለጫ

## ለወቅታዊው  የዓለም ሁኔታ የሚሆኑ ፖሊሲዎች ቀረፃ መርሆዎች ላይ የተደረሰ የስምምነት አቅጣጫ

*አራት የቀድሞ የዓለም ባንክ ዋና የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችን ያካተተ አስራ ሶስት የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች በአሁኑ ጊዜ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አውጪዎች እየገጠማቸው ባሉ ተግዳሮቶች ዙሪያ ውይይት ለማድረግ በሲዊዲን፤ ሳልትስዮባደን (Saltsjobaden) ላይ እ.ኤ.አ ከመስከረም 16-17/ 2016 ዓ.ም ለሁለት ቀናት ተገኝተው ነበር፡፡ ስብሰባው የተዘጋጀው በሲዊዲን ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ እና በዓለም ባንክ አስተናጋጅነት ነበር፡፡ ቡድኑ ያካተታቸው የምጣኔ ሃብት ባላሙያዎች ሳቢና አልኪሬ (ኦክስፎርድ)፣ ፐራናብ ባርድሃን (በርክሌይ)፣ ካአውሺክ ባሱ (ኒው ዮርክ)፣ ሃሩን ቦራት (ኬፕ ታውን)፣ ፍራንኮይስ ቦርግዩግኖን (ፓሪስ)፣ አሽዊኒ ዴሽፓንዴ (ዴልሂ)፣ ራቪ ካንቡር (ኢትሃካ)፣ ጀስቲን ይፉ ሊን (ቤጂንግ)፣ ካሌ ሞኔ (ኦስሎ)፣ ጂን-ፊሊፕ ፕላቶ (ናሙር)፣ ጄሚ ሳቬድራ (ሊማ)፣ ጆሴፍ ስቲግሊትዝ (ኒው ዮርክ) እና ፊን ታርፐ (ሄልሲንኪ እና ኮፐንሃገን) ሲሆኑ፤ በስብሰባው መጨረሻም የቡድኑ አባላት የደረሱበት የጋራ መግባባት ላይ የስምምነት መግለጫ ለማውጣት ወስነዋል፤ መግለጫውም የ"ስቶክሆልም መግለጫ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡*

### 1 የልማት ተግዳሮት

በአሁኑ ወቅት ዓለም በነውጥ ውስጥ እያለፈች ትገኛለች፡፡ ዓለም አቀፍ ኃይሎች ተስፋና ሥጋትን ሰንቀው ይገኛሉ፡፡ በአንድ በኩል ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እየተከሰተ ያለው የቴክኒክ እድገት የኑሮ ደረጃን የማሳደግ/የማሻሻል ተስፋን ሲፈነጥቅ በሌላ በኩል የሰራተኛ መፈናቀልንና የወጣት ሥራ አጥነትን ስጋት አስከትሏል፡፡ የዓለም አቀፍ ንግድ እና ኢንቨስትመንት መስፋፋት ዕድገትን በማፋጠን አብዛኛዎቹን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሀገራት መካከለኛ ገቢ ወደ አላቸው ሀገራት ደረጃ እንዲሸጋገሩ አድርጓል፡፡ ሆኖም ግን በእነዚህ ሀገራት በርካታ ቡድኖች ወደ ኃላ የቀሩበትም ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ በበለጸጉ ሀገራት እንኳ ሳይቀር የሚታይ እውነታ ሲሆን በነዚህ ሀገራትም ብዙዎች በዓለም አቀፍ ትስስር (ግሎባላይዜሽን) ሃይላት በከፍተኛ ደረጃ ተጎጂሆነዋል። በተጨማሪም በግጭትና በጦርነት በሚታመሱ ሀገራት የኑሮ ደረጃ አሽቆልቁሏል፡፡ በአገራት ውስጥ እያደገ የመጣው ኢ-ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል ማህበራዊ ትስስርን እና የኢኮኖሚ ልማትን አደጋ ላይ ጥሏል። የአካባቢ ብክለት/መሸርሸር እና የአየር ንብረት ለውጥ ምድርን አደጋ ላይ የጣላት ሲሆን ይህንን የተጋረጠ አደጋ ለማስወገድ የተቀናጀ ዓለም አቀፋዊ እርምጃ ይጠብቃል፡፡ ፈጣን የከተማ ዕድገት በአንድ ቦታ ከመሰባሰብ (agglomeration) የሚመነጭ የምርታማነት እድገትን ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆንም፤ የከተማ ቆሻሻ መንደሮች መስፋፋትን እንዲሁም የድህነት እና ግጭት ችግሮችን ሊያባብስ ይችላል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የትኛቸውም በአለም ላይ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ የመጣውን የገቢ መጠን እንዲሁም የጤና እና ትምህርት መሻሻል እመርታዎች ማሳነስ/መጋረድ አይቻላቸውም። እነዚህን ስኬቶች እያከበርን ፖሊሲ አውጪዎች ያለጥርጥር ሊገጥሟቸው የሚችሉ ተግዳሮቶችን/ፈተናዎችን አሻግረን እንመለከታለን። ለእነዚህ ተግዳሮቶች ስኬታማ መልስ መስጠት የሚቻለው የዓለም ኃይሎችን በመግራት ለልማት በመጠቀም እና ከአደጋዎች ይልቅ የዕድገት ተስፋን ወደሰነቁ አቅጣጫዎች መምራት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን በመንደፍ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ የልማት

ፖሊሲ ግቦች ላይ ግልጽ ራዕይ ከመፈለጉም በተጨማሪ ለረዥም ጊዜ ከተካበቱት የምጣኔ ሀብት ጽንሰ/ንድፈ ሀሳቦች እና እስታቲስቲካዊ ትንታኔዎች እንዲሁም ካለፉት ስኬቶችና ስህተቶች መማርን ይጠይቃል፡፡

አንዳንድ በጣም የተለመዱ ኢኮኖሚያዊ ምክረ ሃሳቦች ዋጋ እንዳልነበራቸው አሁን እሙን/ግልጽ ነው። ፖሊሲ አውጪዎች እንደ የበጀት ሚዛንን ጠብቆ መቆየት፣ የዋጋ ግሸበትን ለመቆጣጠር የገንዘብ ፖሊሲን መጠቀም፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ማስጠበቅ እና ከዚያም የተቀረውን ለገበያው ስርዓት መተው በሚሉ አይነት ቀላል የፖሊሲ መመሪያዎች ላይ መመካት አይችሉም። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ/አካሄድ ለድሆች የሚንጠባጠብ ዕድገት እንዲሰፍን ያደርጋል የሚለው ታሳቢ የሚያሳምን መላምት አይደለም። በእርግጥም በእኛ እምነት አሁን ያለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ይህን አይነት ጊዜው ያለፈበት ምክር በጥብቅ ከመከተል የመጣ ዕዳ ነው።

ይህ መግለጫ የፖሊሲ መመሪያ የሚሆን ንድፍ ሃሳብን የሚያስቀምጥ ሳይሆን በአገር-ደረጃ የሚወጡ ፖሊሲዎችን መልክ ለማስያዝ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውይይቶችን እና የጋራ ፖሊሲዎችን ቀረጻ ያበረታታሉ ብለን ያመንባቸውን መርሆች ስብስብ የሚያስቀምጥ ነው። እነዚህ መርሆዎች ዛሬ በፍጥነት እየተለዋወጠ እና ወደ አንድ መንደርነት እየተቀየረ （ግሎባላይዝድ እየሆነ） ለመጣው ዓለም አስፈላጊነታቸው ከመቼውም ጊዜ በላይ እየጨመረ ነው።

## 2 ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በራሱ መጨረሻ አይደለም

ምንም እንኳን ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገትን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ብናምንም፤ ያ በራሱ የመጨረሻ ግብ ሳይሆን የተሻሻለ የጤና፣ የትምህርት፣ የሥራ እድል፣ የኑሮ ዋስትና እንዲሁም ፍጃታን ያካተቱ የተለያዩ ማህበራዊ ዓላማዎችን ስኬታማ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሀብቶችን እንደ መፍጠሪያ አንድ መንገድ ነው፡፡የግለሰብ ደህንነት ዘርፈ ብዙ ነው፤ እናም ፖሊሲ ገቢን ብቻ ሳይሆን ኅብረተሰቡ ዋጋ በሚሰጣቸው ዘርፎች ላይ ሁሉ ማሻሻያ ለማድረግ ማለም ይገባዋል። ለምሳሌ ያህል ለሁሉም የቅድመ-ትምህርት ቤት ልጆች የተሻለ ምግብ ማቅረብ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ እና እነዚህም በሚገባ ሊተገበሩ ከሚችሉ ውስጥ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። ትክክለኛ ፖሊሲዎች በቦታው እስከሌሉ ድረስየጠቅላላ አገር ውስጥ ምርት እድገት ከአካባቢ እና ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት መመናመን ጋር የተያያዙ የደህንነት ገጽታዎችን ጨምሮ እነዚህን የደህንነት ዘርፎችን ዋጋ በማስከፈል ሊመጣ ይችላል።በተጨማሪም አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በራሱ ተጋላጭ ቡድኖች ላይ የሚደረጉ ጨቋኝ ደንቦች እና አድሏዊ ልማዶችን ማስቀረት ሊያቅተው እንደሚችል ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። እነዚህ ጉዳዮች አብዛኛውን ጊዜ ሆን ተብሎ የሚደረግ ጣልቃ ገብነትን ይፈልጋሉ።

ለሁሉም ኢኮኖሚዎች （አገራት） ተገቢ/ተስማሚ የሆነ አንድ ነጠላ የሐኪም ትእዛዝ ሊኖር እንደማይችል የማመንን አስፈላጊነት እንገነዘባለን። ልክ እንደ ታሪክ ባህላዊ እና ማህበራዊ አውዶች ይለያያሉ። ይህም በተለያዩ ኅብረተሰቦች የተለያዩ ምኞቶች እንዲኖሩ ከማድረጉ በተጨማሪ ምን(የትኛው ፖሊሲ) መሥራት ይችላል የትኛውስ ሊሰራ አይችልም የሚለውን በመወሰን ረገድ የራሱን ሚና ይጫወታል። ቀደም ሲል ለሁሉም አገራት አንድ ወጥ ፖሊሲ ኮድ （በአንድ

ሃብታም አገር የተቀመረ/የተቀረጸ) የማዘዝ ዝንባሌ ነበር።ሁላችንም ትኩረት ልንሰጥባቸው የሚገቡ ሰፊ የፖሊሲ መርሆች ያሉ ቢሆንም ለብዝሃነት እና ለፖሊሲ ዐውድ-ተኮርነት ቦታ ሊሰጥ ይገባል።

## 3 ልማት አካታች መሆን አለበት

ፖሊሲ የልማትን ማኅበረሰባዊና እና ኢኮኖሚያዊ አካታችነት ለማረጋገጥ እገዛ ሊያደርግ እንደሚገባ እና በጾታ ሆነ፣ በጎሳ ወይም በሌሎች ማህበራዊ መገለጫዎች የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ኋላ ትቶ መሄድ እንደሌለበት እናምናለን። ከፍተኛ ማጣትን በተመለከተ ከተለያዩ ማህበረሰባዊ ደህንነት ዘርፎች አንጻር የተለየ ትኩረት መኖር አለበት፤ በተለይም ደግሞ ከብዙ የደህንነት ገጽታዎች አንጻር በተደራራቢ ችግሮች የሚሰቃዩ ግለሰቦች ላይ። ነገር ግን በጣም የተቸገሩ ላይ ማተኮር ብቻ ግን በቂ አይደለም። በሀብታም እና ድሃ እንዲሁም በዋና ዋና ማህበራዊ ቡድኖች መካከል ያለው ክፍተትም በጣም አስፈላጊ ነው።ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ሁኔታ እየናረ የመጣው የገቢ እና ሀብት ልዩነት እና እንደ ጤና እና ትምህርትን የመሳሰሉ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ከማግኘት አንጻር የተስተዋለው የዕድሎች ልዩነት ደረጃ ከስነ ምግባር አንጻር ተቀባይነት ሊኖረው የማይችል፣ ማህበራዊ ትስስርን የሚያዳክም እና የፖሊሲን በልሂቃን ቁጥጥር ስር መዋልን እና መዘወርን በማማባስ የኑሮ አለመመጣጠኑን የሚያባብስ ነው። ከፍተኛ ልዩነት የድሆችን ድምጽ በመዝረፍ የዴሞክራሲንም መዳከምን ያስከትላል። ሴቶችን እና በታሪክ መድልዎ የደረሰባቸው ቡድኖችን ማብቃት በራሱ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ከመሆኑም ባሻገር ለኢኮኖሚ ቅልጥፍና (efficiency) አሳማኝ መሰረት ይጥላል። የፖለቲካ አለመረጋጋት እና ማህበራዊ ግጭት በሚኖርበት ጊዜ ልማት የሚቻል አይደለም፤ እና የልማት ፖሊሲዎች አካታች ባልሆኑበት ሁኔታ ማህበራዊ ግጭቶች መቀስቀሳቸው አይቀርም። በአጠቃላይ አካታች ልማት ብቸኛው የማኅበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ዘለቄታ ያለው የልማት አይነት ነው።

## 4 የአካባቢያዊ ዘላቂነት አስፈላጊ እንጂ ምርጫ አይደለም

ምንም እንኳን እንደ እያንዱ አገር እና አህጉራዊ ዐውድ/ነባራዊ ሁኔታ በተለያየ መንገድ የሚካሄድ እና የሚተገበር ቢሆንም የልማት ፖሊሲ ቀረጻ የአካባቢያዊ ዘላቂነትን ዋነኛ አላማው አድርጎ መውሰድ አለበት የሚል እምነት አለን። ይህ በቀጥታ ከአካባቢያዊ መንሳቆል ጋር የተያያዘ ነው፤ የገቢ እድገት በተናጠል ስለ ማህበረሰባዊ ደህንነት እና እድገት/መሻሻል ሓሰተኛ አመላካች ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፤ በሀብት ዙሪያ የሚደረግ ውድድር እና ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የተዛመደ ፍልሰት የደህንነት ስጋት ከመፍጠሩም ባሻገር ወደ ግጭቶች በማምራት ልማትን ያቆረቁዛል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥ ለምድራችን ህልውና የረጅም ጊዜ ስጋት ሲሆን በአንፃሩም በብዙ አገራት ለኑሮ፣ ለግብርና እና ለመኖሪያ ከአጭር-እስከ መካከለኛ ጊዜ ስጋት ሆኗል። ይህንን ችግር የመግታት ጥረቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ሲሆን፤ ከነገሮች ጋር ተቻችሎ የመኖር (adaptation) ፖሊሲዎች በብሔራዊ እና በአካባቢ ደረጃ ንቁ ጣልቃ ገብነት እና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ችግሮች ነፃ ገበያ ይፈታቸዋል ተብለው ሊተዉ የማይችሉ ችግሮች ናቸው። በዚህረገድ የመንግስት የቁጥጥር ጣልቃ ገብነት እንዲሁም በአገሮች መካከል የተቀናጀ ፖሊሲ መኖር የግድ አስፈላጊ ነው።

## 5 የገበያን የመንግስትን እና የማህበረሰብን ሚዛን መጠበቅ አስፈላጊነት

ከእነዚህ ዓላማዎች እና የዓለም ማህበረሰብ ላይ ከተጋረጡት የዓለም አቀፍ ችግሮች/ተግዳሮቶች አንፃር የልማት ፖሊሲ በገበያ፣ በመንግስት እና በማህበረሰብ መካከል ጥንቃቄ የተመላበት ሚዛን ጠብቆ መገንባት አለበት። ገበያዎች ራሳቸው የተነሱበትን ውጤታማ የኢኮኖሚያዊ የሃብት ድልድል አላማ ለማሳካት ቀልጣፋ የሆነ የደንብ ማዕቀፍ የሚያስፈልጋቸው ማኅበራዊ ተቋማት መሆናቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም፤ የገበያ ስረዓት የኢኮኖሚያዊ ቅልጥፍናን ማምጣት ይችላል ብንል እንኳን፤ ፍትሃዊነትን እና አካታችነትን የማምጣት/የማስገኘት ምንም አይነት ተፈጥሯዊ ዝንባሌ የለውም። አሁን እንደምናውቀው ረሃብ እና የነፃ ገበያ ቅልጥፍና ተኳሃኝ ናቸው። የገንዘብ ቀውስን እና ተቀባይነት የሌለው ደረጃ ላይ የደረሰውን የእኩልነት መዛበት እና ዘላቂነት አለመኖር ጨምሮ በአሁኑ ወቅት ዓለም እያጋጠሟት ላሉ የተለያዩ ኩነቶች ባለፉት ሩብ ምዕተ አመታት የታየው ወደ ነፃ ገበያ ስርዓት የመዞር አዝማሚያ ምክንያት ነው።

የገበያ ስርዓት በራሱ ሊያከናውናቸው የሚችላቸው ነገሮች ገደብ እንዳላቸው የምናውቅ ሲሆን መንግስትም እራሱ በቅልጥፍና ሊሰራ እንደሚያስፈልግ እንገነዘባለን። አገራት ከገበያ ስርዓት ባሻገር ሊከተሏቸው የሚችሉ በርካታ መንገዶች አሉ። በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የመንግስት አካላት እና እንደ የህብረት ስራ ማህበራት፣ ማህበራት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የመሳሰሉ የተለያዩ የሲቪል ማህበራት የራሳቸውን ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።መንግስት የገበያ ስርዓቱ ወይንም ማህበረሰቡ በተሻለ ሁኔታ የሚሰራቸው ተግባራት ላይ መሳተፍ የለበትም። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ተቋማት ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ አብረው ይሰራሉ። በአስከፊ ድህነት ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ደህንነት በህብረተሰቡ ደረጃ በሚገኙ የአካባቢ ቡድኖች በተሻለ መልኩ የሚስተናገድባቸው አግባቦች አሉ። ምንም እንኳን የአካባቢ የማህበረሰብ ተቋማት የጎታች ሃይሎች መጠቀሚያ ሊሆኑ እንደሚችሉ የታወቀ ቢሆንም፤ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማህበራዊ ትስስርን በማበረታታት እና በማስጠበቅ ረገድ ወሳኝ ሚና ዓላቸው።

መንግስት የጨዋታውን ህጎች ከማውጣት እንዲሁም የገበያ ስረዓቱን እና ማህበረሰቦች የሚያብቡበትን እና የሚጎለብቱበትን የቁጥጥር ማዕቀፍ ከማቋቋም ወይንም ከመገንባት አንፃር የሚኖረው ሚና እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ለማስረገጥ እንወዳለን። የተሻሉ የጨዋታ ህጎችን ተከትሎ  የሚመጣ የማህበራዊ ትስስር መጠናከር እና ተአማኒነት ልዩነትን ከመቀነስ በተጓዳኝ እድገት እና ደህንነትን በሁሉም መልኩ ያስፋፋል። በተጨማሪም መንግስት የገበያ ስርዓቱበተገቢ ሁኔታ በማይሰራባቸው ቦታዎች ላይ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በዚህ ረገድ ፋይናንስ፣ ጤና እና የአካባቢ አጠባበቅ እንደ ዋና ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተመሳሳይ መልኩ ግልፅ በሆነ መልኩ አሳታፊነትን በሚሹ፤ ለምሳሌ እንደ ሴቶችን ማብቃት፣ ተጋላጭ ቡድኖችን መጠበቅ እና ኢ-ፍትሃዊ የሆነ የገቢ እና የሃብት ክፍፍል ችግርን ምፍታትን የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ መንግስት ጉልህ ሚና ይኖረዋል። ከዚህ ባሻገር የኢንዱስትሪ እንዲሁም ውጤታማ የግብርና እና የአገልግሎት ዘርፍ ፖሊሲዎችን በመቅረጽ ረገድ መንግስት የሚጫወተው ሚና ይኖረዋል። መንግስት እየጨመረ የመጣውን የልዩነት ኡደት መከላከል አለበት። ይህ ካልሆነ የመንግስት ተቋማት እና የጨዋታው ህግ በግለሰብ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ በማድረግ ማህበራዊ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች እንዲጠናከሩ ያደርጋሉ።

## 6 የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ማስፈን

አብዛኞቹ የተለመዱ የፖሊሲ ምክሮች የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ላይ ያተኮሩ ነበሩ። ከፍተኛ የኢኮኖሚ መረጋጋት ያላቸው አገራት ደህንነትን በይበልጥ ከማሻሻል ጋር የተያያዘ ከፍተኛ እድገት በማምጣት ረገድ ስኬታማ ናቸው። የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ኢኮኖሚው በማይዋዥቅ መሰረት ላይ እንዲቆይ ፖሊሲዎችን መቆጣጠርን እና ዛሬ የሚወሰዱ የፖሊሲ እርምጃዎችን - በተለይም የበጀት እና የውጭ ፋይናንስ/ገንዘብ ፍሰት ዘላቂነትን ከማረጋገጥ አንፃር የሚወጡ ፖሊሲዎችን - የረዥም ጊዜ እንድምታ ላይ ትኩረት መስጠትን ያካትታል። አገራት ጠንካራ እድገት በሚያስመዘግቡባቸው ወቅቶች የበጀት አቅማቸውን በመገንባት አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ወቅት ይህንን ሃብት እንደ መፍትሄ ለመጠቀም ዝግጁ ሆነው መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ይህም ሆኖ ሳለ ምንም እንኳን የረዥም ጊዜ የበጀት ስነ-ስርዓት ቁጥጥር መኖር አስፈላጊ ቢሆንም እንዲሁም የተለመደው የምጣኔ ሃብት አስተሳሰብም እዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት መስጠቱ ትክክል ቢሆንም፤ የፖሊሲ አውጪዎች አብዛኛውን ጊዜ በጀትን የማመዛዘን ጉዳይ ላይ ከልክ ያለፈ ትኩረት ሲሰጡ ይስተዋላል።

የበጀት ማነቃቂያዎች እና የመንግስት መዋእለ ንዋይ ፍሰት ከኢኮኖሚ የመቀዛቀዝ ወጥመድ ለመላቀቅ ብዙውን ጊዜ ወሳኝ መሆናቸውን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ቢሆንም እነዚህ እርምጃዎች አስተማማኝ የሚሆኑት የእዳ ጫናውን እንዲሁም በኢኮኖሚው ውስጥ የገንዘብ ፍሰትን ተከትሎ የሚመጣውን የዋጋ ግሽበት መቆጣጠር እስከተቻለ ድረስ ብቻ ነው። የመንግስት መዋእለ ንዋይ ፍሰት መሰረተ ልማትን እና አረንጓዴ ቴክኖሎጂን ለመገንባት አስፈላጊ ሲሆን ይህም ለወደፊት የግሉን ዘርፍ መዋለ ንዋይ ፍሰት ከመሳብ አኳያ የረዥም ጊዜ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም የማክሮ ኢኮኖሚ ጥንቃቄ (macro-prudential) እርምጃዎኛ ድንገተኛ እና ኢ-ታእማኒ የሆኑ የልማት ክስተቶች (bubbles) መፈጠርን በማስቀረት እንዲሁም ያልተረጋጋ የካፒታል ፍሰትን እና ከልክ ያለፈ የውጭ እዳ መቆለልን በመከላከል ለገንዘብ ፖሊሲ ድጋፍ ያደርጋል።

## 7 የዓለም አቀፍ ቴክኖሎጂ እና ተበላላጭነት ተጽእኖን መቆጣጠር

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ያለው ከፍተኛ የቴክኖሎጂ መሻሻል በፖሊሲ ነደፋው ሜዳ ላይ የተለየ ተግዳሮትን ፈጥሯል። አዲስ ቴክኖሎጂ አለም አቀፍ የሰው ሃይልን በማስተሳሰር በታዳጊ አገራትያሉ ሰራተኞች ሌላ ቦታ መሄድ ሳያስፈልጋቸው ለአለም አቀፍ ገበያው እና ሸማቾች መስራት አስችሏቸዋል። ይህ ሁኔታ ለሰራተኞች አዳዲስ እድሎችን የፈጠረ ቢሆንም በየአገራቱ ውስጥ ያለውን የገቢ አለመመጣጠን እና ኢ-ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን አባብሷል። ከፍተኛ ገቢ ባላቸው አገራት ውስጥ ይህንን ጉዳይ ለታዳጊ አገር ሰራተኞች ፍላጎት/ጥቅም ሲባል ባደጉ አገራት ውስጥ ያሉ ሰራተኞችን ጥቅም የማጉላላት አይነት በሰራተኞች መካከል ያለ ተቃርኖ አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ እየጨመረ መጥቷል። ይህ አሳዛኝ ጉዳይ ነው። ችል የተባለው እውነታ ግን ይህ በአብዛኛው በሰራተኛው እና በካፒታል መካከል ያለ ተቃርኖ መሆኑን ነው። የራስ ሰር ቴክኖሎጂ（automation）መስፋፋት እና የሮቦቶች በሰፊው ጥቅም ላይ መዋል እንዲሁም የሰራተኖች ገበያ አለም አቀፋዊ መሆን（ግሎባላይዜሽን）፤ ሠራተኞችን ማፈናቀል ብቻ ሳይሆን የሰራተኛውም ገቢ በኮርፖሬሽኖች እና የማሽን ባለቤቶች ከፍተኛ ትርፍ ይተካል። እነዚህን አሳሳቢ መዘዞች እንደ ዓለም አቀፋዊ በሰራተኞች መካከል ያለ ተቃርኖ መቁጠር ሳያስፈልግ መፍትሄ ሊሰጣቸው ይገባል።

ይህ ሶስት አስገዳጅ/አንገብጋቢ ፖሊሲዎችን ይፈጥራል። በመጀመሪያ በሰው ሃይል ካፒታል ላይ ንዋይ በማፍሰስ ለቴክኖሎጂ አጋዥ በሆነ መልኩ የሰራተኛዉን የስራ ችሎታ መጨመር እና በዚያውም የሰራተኛውን ገቢ ከቴክኖሎጂ እድገት ጎን ለጎን ማሳደግ አለብን። ሁለተኛ በአገራት ውስጥ የገቢ ሽግግሮችን የምንከውንበት አዳዲስ ዘዴዎችን/መሳሪያዎችን መፍጠር አለብን። ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ውስጥ የደሞዝ ድርሻ መቀነስ የማይቀር የቴክኖሎጂ እድገት ውጤት ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ይህንን ኡደት ለመላቀቅ/ለመስበር መንግሥታት ግብር እና ትርፍ-መጋራት ስርዓት መፍጠር አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ የጨዋታውን ደንቦች/ህግጋት መፍጠር - ለምሳሌም የሠራተኛውን የመደራደር አቅም ማሳደግ የሚችሉ እና በህብረተሰቡ ውስጥ እና ድርጅቶች ውስጥ ያላቸውን ተደማጭነት የሚጨምሩ ጠንካራ የውድድር ህጎች እና የሠራተኛ መተዳደሪያ ደንቦችን ማውጣት አለባቸው። በመጨረሻም ይህ ልዩ የሆነ የብዙ አገራትን ፍላጎትን ያቀፈ የፖሊሲ ትግበራን አስፈላጊነት ያጠይቃል። በአገራት መካከል ያለዉን የፖሊሲ መጣጣም እና የሃብታሞቹን እና ያደጉትን አገራት ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ በአለም አቀፍ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ድምፅ የሚነፈጋቸውን የታዳጊ አገራትን ጨምሮ የሁሉንም አገራት ፍላጎቶች የሚያንፀባርቁ/የሚያካትቱ ፖሊሲዎችን ወደፊት የመግፋቱን ሃላፊነትም በአለም አቀፍ ተቋማት ላይ ያሳርፉል።

## 8 የማህበራዊ ደንቦች እና አመለካከቶች አስፈላጊነት

የተለመደው የምጣኔ ሃብት አስተሳሰብ በአብዛኛው ማህበራዊ ደንቦችን እና አመለካከቶችን በኢኮኖሚያዊ ሕይወታችን ውስጥ ምንም ፋይዳ እንደሌላቸው አድርጎ ይቆጥራል። እያደገ የመጣው የምርምር አካል እንደሚያሳየው ግን ይህ ትክክል አይደለም።ባህሎቻችንና እሴቶቻችን በራሳቸው አስፈላጊ/ጠቃሚ ከመሆናቸውም ባሻገር ኢኮኖሚው እንዴት እንደሚሰራ ይወስናሉ። ሰዎች እርስ በእርስ የሚተማመኑበት ማህበረሰብ ሰዎች እርስ በእርስ ከማይተማመኑበት ማህበረሰብ በተሻለመልኩ ይሰራል። አንድ አይነትየምርጫ ስብስቦችን በተለያየ መልክለሰዎች ማቅረብ - ለምሳሌ በተለያየ ቅደም-ተከተል ወይም በተለያየ ገዢ (default) አማራጭ -ሰዎች በሚመርጡት ምርጫ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። መንግስታት እንደዚህ ያሉ አዳዲስ እይታዎችን እና ዘዴዎችን ፕሮግራሞቻቸውን እና አገልግሎ ታቸውን በተቻለ መልኩ ለማስኬድ መጠቀም ይኖርባቸዋል። በግሉ ዘርፍ ያሉ ተቋማት እና ድርጅቶች ስለሰው ልጅ ስነልቦና እና ማህበራዊ ዝንባሌ ያላቸውን እውቀት ፍላጎታቸውን እና ትርፋቸውን ለማሳደግ ሲጠቀሙበት እና ብዙ ጊዜም ሲመዘብሩት ቆይተዋል። መንግስታት የትምህርት እና የጤና አገልግሎትን በተሳካ መልኩ ለመስጠት/ለማቅረብ እና ግብርን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለመሰብሰብ ከፈለጉ ለማህበራዊ ልማዶች ያለውን የተሻሻለ ግንዛቤ የወል/የጋራ ጥቅም ከሚሻ የፖሊሲ አወጣጥ ጋር ማቆራኘት ያስፈልጋል። ማህበራዊ ደንቦች እና አመለካከቶች ሙስናን ከመግታትም ረገድ ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ማህበራዊ ደንቦች እና አመለካከቶች የእያንዳንዱ ማህበረሰብ ታሪክ እና ልምድ ውጤት እንደ መሆናቸው መጠን ይህ አይነቱ ጉዳይ የአገራትን ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ የማስገባትን አስፈላጊነት በይበልጥ ከሚፈልጉ ጉዳዮች አንዱ ነው።

## 9 የዓለም አቀፍ ፖሊሲዎች እና የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ኃላፊነት

የዓለም አቀፍ ኃይላት ብሄራዊ መንግስታት ያሏዋቸውን ከፍተ የልማት ፖሊሲ አማራጮች የመወሰን ሚና እየጨመረ መጥቷል። እነዚህ ሃይላት የራሳቸውን እድሎች እና ማነቆዎችን/መሰናክሎች የሚያቀርቡ ሲሆን እነሱም በተራቸው በሌሎች አገራት ውስጥ በሚወሰዱ እርምጃዎች ይወሰናሉ።

ከፍተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ ያለው የገንዘብ ፖሊሲ ወደ ታዳጊ አገሮች ሊኖር የሚችለው የካፒታል ፍሰት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። በ2008ቱ የገንዘብ ቀውስ በበቂ ሁኔታ ለመረዳት እንደተቻለው በበለጸጉ አገራት ውስጥ ያሉት የፋይናንስ ቁጥጥር ፖሊሲዎች ምንም እንኳን በመጀመሪያው ደረጃ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት በእራሳቸው ላይ ቢሆንም በስተመጨረሻ በታዳጊ እና በማደግ ላይ ባሉ አገራት ላይ ተፅዕኖ መፍጠራቸው አይቀሬ ነው። ከታክስ መሸሸጊያ አገራትን በተመለከተ የሚወጡ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች የሁሉንም አገራት በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አገራት ለአሳታፊ እና ዘላቂ ልማት የሚውል የቀረጥ ገቢ ለመሰብሰብ ያላቸው አቅም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይፈጥራል። የአንዱ አገር የአለም አቀፍ ንግድ ፖሊሲዎች የሌሎችን አገራት የወጪ ንግድ ተስፋ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል። በአደጉ አገራት ያለው የፍልሰት ፖሊሲ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አገራት ዜጎች ራሳቸውን ለማሻሻል እንዲሁም የአገራቸውን ልማት በገንዘብ እና በእውቀት ሽግግር ለማገዝ/ለመደገፍ ያሏቸው አማራጮች ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል። በእነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ እያንዳንዱ አገር አሁን አለም በተሳሰረበት በዚህ ወቅት በሌሎች አገራት ላይ የዋስትና ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህም በመሆኑ ሁሉም አገራት እጅግ የተነፈጉ የአለማችን ዜጎችን የልማት እድሎች ከግምት ውስጥ የማስገባት እንዲሁም የማስፋፋት ሃላፊነት አለባቸው።

የተለያዩ አገራትን ያቀፉ ስምምነቶች እና ተቋማት የጊዜያችንን አንዳንድ ብርቱ ችግሮችን ለመፍታት በጣም አስፈላጊ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህን ተቋማት እና ስምምነቶች መገንባትና በሚገባ መጠበቅ በጣም አስቸጋሪ እየሆነ ይታያል።በአየር ሁኔታ ለውጥ ዙሪያ ፓሪስ ላይ የተደረሰው ስምምነት ጥሩ ሆኖ ሳለ ሁሉም አገራት በልቀት ላይ የገቡትን ስምምነት በቁርጠኝነት መተግበርን ገና አለም እየጠበቀ ያለው ጉዳይ ነው።እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አገራት በአየር ለውጥ ዙሪያ ለሚያደርጉት ጥረቶች (ችግሮችን የመቅረፍ እና ተቻችሎ መኖር) ከፍተኛ ገቢ ካላቸው አገራት የገንዘብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። ከቅርብ አመታት ወዲህ ከመደበኛ(ከተለመዱት) ምንጮች የሚገኘው የልማት እርዳታ መቀነስ ያሳየ ሲሆን ከአስርተ አመታት በፊት የአለም አቀፍ ማህበረሠብ የተስማማበትን የ 0.7 በመቶ የኦፊሲዬላዊ የልማት እርዳታ ግብ መምታትን እንኳን ወደ ጎን ብንተወው አዳዲስ የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን የልማት ተቋማት እንደ አሸን መፍላት ተስተውሏል። የዓለም አቀፍ ማህረሰብ እርዳታ በቀጥታ ለታዳጊ አገሮች እና በእነዚህ አገራት ውስጥ ለሚገኙ የተረሱ ወይም የተገለሉ ቡድኖች መድረሱን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት። በተጨማሪም ታዳጊ አገራት በአለም አቀፍ ተቋማት የአስተዳደር መዋቅሮች ውስጥ በሚገባ መወከላቸውን በማረጋገጥ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና ጉባኤዎች የእነዚህን አገራት ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 10 ወደፊት የማየት ሁኔታ

የልማት ተግዳሮቶችን ከመፍታት አኳያ አገሮች የገበያን የመንግስትን እንዲሁም የማህበረሰቡን ሚዛን የጠበቁ እና በተግባር ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችን ቢከተሉ እንዲሁም የአለም አቀፉ ማህበረሰብ የአለም አቀፍ ሃይላት የሚፈጥሩትን ተግዳሮቶች

ለማስታገስ እና አዳዲስ የተፈጠሩ እድሎችን ለመጠቀም ተባብሮ ቢሰራ አለም እያየ ያለውን የቴክኖሎጂ እመርታ በጣም የተቸገሩትን ጨምሮ ሁሉን አቀፍ ወደ ሆነ የደህንነት ብልጽግና ወይም  እድገት መተርጎም ይቻላል።የጋራ ብልጽግና የተጎናጸፈ አለም መገንባት ወይም ማሳካት እንችላለን። ያለፉት ስህተቶች እና ስኬቶች አገራዊና አለም አቀፋዊ ፖሊሲዎች ሊያስነድፉ የሚችሉ የመርሆች ስብስብን ይጠቁማሉ።አሁን እነዚህን መሰረታዊ መርሆች/ስርአቶች ስልታዊ በሆነ መልኩ በመጠቀም ለልማት የሚሆኑ የኢኮኖሚ ፖሊሲች የሚነደፉበት ወቅት ነው።